# የብርሃኑና አንዳርጋቸው የፓልቶክ ፀረ ወያኔ ዛቻ
# ወይስ የወያኔ ፕላን ቢ

ጉድ በማያልቅባት ኢትዮጵያ ወያኔያዊው ግፍና ድራማ ላፍታም ሳያቋርጥ እንደቀጠለ ለመሆኑ ለወያኔ አልንበረከክ ያለውና ኢትዮጵያዊ አንድነትን የሙጥኝ ያለው የወጣቱ ፕሮፌሰር አሥራት የቴዲ አፍሮ ለተራዘመ ጊዜ ወደ ወህኒ መወርወር ትኩስ ምሥክር ሲሆን የቴዲን ግፍ ለማረሳሳት በሚመስል ወያኔ የቀድሞ ቅጥረኛውን ታምራት ላይኔን ፈታሁ የሚል አስቂኝ ድራማም እየሰራ ነው::

በሌላ በኩልም በውጭ ተበትኖ ያለውና ራሱን በተቃዋሚነት የፈረጀውም ክፍል ደግሞ የበኩሉን ድራማና ቢዝነስ ተያይዞታል:: ለዚህ ደግሞ ግንቦት የተባለው ድርጅት መሪዎች ነን የሚሉት ግለሰቦች የፓልቶክ መወራጨት አንዱ ምሳሌ ነው::

ይኸው የሰሞኑ የፓልቶክ ግርግር በደርግ ዘመን አንዳንድ ከሀገር ለመውጣት ጉገት የነበራቸውን ወጣቶች ስሜት የተረዱ አጭበርባሪዎች ይጠቀሙበት የነበረውን ድራማ ያስታውሳል:: ሁላችንም እንደማንዘነጋው በወቅቱ ከሀገር ለመውጣት በተለይም ወጣት ሆኖ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደነበር ነው:: ይህን ሁኔታ በመጠቀምም ጩሉሌዎቹ የእለት የበርጫ ወጪያቸውን ለማግኘት የማያደርጉትን እንደሚያደረጉ ከኤምባሲዎች ጋር ግንኙነት እንዳለቸውና ባለሥልጣን እንደሚያውቁ በመግለፅ ቪዛ ማስመታት ካገር ማስወጣት እንችላለን በሚል ቅጥፈት የብዙዎችን ኪስ ያራቁቱ ነበር:: አንዳንዶቹማ ጉዳዩን የበለጠ ለማሳመንም ሀገር እስከማስመረጥ ይደርሳሉ ይታያችሁ ይህ ሁሉ የሚሆነው ባንድ ቀን ጀምበር ነው:: አንዱ ጣሊያን፤ ሌላው ጀርመን፤ አቴንስ፤ ከጠፋ ከጠፋ ናይሮቢም ቢሆን ምንም አይደል ብቻ ከደርግ ልገላገል ይላቸዋል:: “ለአስወጪው” ጮሌ ጫቱም ሲጋራውም ሌላውም ይደረግለታል… ጮሌውም አውሮፓ በጄ ነው አፍሪካ ግን ኮንታክቱ ለጊዜው ዩሮፕ ስለሄደ እስኪመለስ መቆየት ከቻላችሁ ችግር የለም ብሎ የበለጠውን የሰዉን ቀልብ አነሳስቶት በምርቃና ፈረስ ሰዉን ሁሉ አውሮፓ ላውሮፓ ሲያዞረው አምሽቶ የሚፈልገውን ካገኘ በኋላ እንግዲህ ፓስፖርታችሁን አዘጋጁ የሚል ማሳሰቢያ ብጤ በመስጠት ለሚቀጥለው ጊዜ በቀጠሮ እንገናኝ ብሎ ፈትለክ ይላል:: ውሎ አድሮም ምርቃናው ተሰብሮ ተስፋውም ተኖ ግለሰቡም የውሀ ሽታ ሆኖ ይቀራል:: ለነገሩ የነዚህ እዳው ገብስ ነው::

ሰሞኑን የመርሻ ጌታቸው ዘላን አንጀኞች ብቸኛ እስትንፋስ በሆነችው ፓልቶክ ሩም ብርሃኑ ነጋ፤ ቀደም ሲል ደግሞ አንዳርጋቸው ፅጌ ከረንት አፌይር በተባለው ሩም በተከታታይ ሳንቅም አስመርቅነውን በምርቃና ፈረሳቸው አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ደጃፍ አድርሰው እየመለሱን ነው:: የሚገርመው የሁለቱን ጓደኞሞች ንግግር ለሰማ አንድ አይነት የሸወዳ መጽሐፍ እንዳነበቡ መረዳት አያዳግትም ምንም እንኳ ብርሃኑ አላስዋሽ ያሉ ታዳሚዎች በጥያቄ አጣድፈው (አጋልጠውት ማለት ይሻላል) ሰአት ደርሶብኛል ቀጠሮ አለብኝ ብሎ ፈርጥጦ እስኪያመልጥ ቢያስገድዱትም::

ሁለቱም ግለሰቦች የሚደሰኩሩት ወያኔን <u>በስድስት ወር</u> ውስጥ አሸቀንጥረው እንደሚያባርሩት ፤ለአመታት የሚጠብቅ ትእግስትም ሆነ ጊዜ እንደሌላቸው ነው:: የብሶት መለኪያው ህዝብ ሳይሆን እነሱ መሆናቸው ነው:: “እኛ ለውይይትና ለቀልድ ጊዜ የለንም “ዊ አር ሲሪየስ” ወስነናል፤ መሮናል፤ ወያኔን እናንተ አታውቁትም …ወዘተ…ወዘተ በሚሉ የውሸት ብስጭት የተቀላቀለበት ቀረርቶ ሲያሰሙ እውነተኛ ማንነታቸውን ለማያውቅ ቀርቶ የሚያውቃቸውን እንኳ ያጠራጥራሉ:: በቀረርቶዋቸው ጣልቃም ከናንተ የምንፈልገው ሪሶርስ ብቻ ነው ወያኔን ‘መቦጫጨቁን’ ለኛ ተዉት ይላሉ:: ለመሆኑ ይህን ማድረግ ከቻሉ ለምን እስካሁን ዝም

አሉን? ይኸው አሁን እንደምንሰማው በፕሌት 500.00 ዶላር የሚያወጣ የ’ሪሶርስ’ ማሰባሰብ ዘመቻ ጀምረዋል::

ነገሩ ሁሉ አልዋጥ ያላት አንዲት የፓልቶኩ ተሳታፊ ብርሀኑን ባለቤትህ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያንተን ቢዝነስ በስፋት እያካሄደች አንተ እዚህ ቁጭ ብለህ በትጥቅ ትግል በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወያኔን እደመስሳለሁ ትላለህ እናንተ ሰዎች አሁንም እየቀለዳችሁብን ነው? የሚል ዱብ እዳ ሳያስበው ስታወርድበት ለጥያቄው የሚሰጠው መልስ ጠፍቶት በድንጋጤ ሲንተባተብና ጥያቄውን ለራሱ ሲደጋግመው ይሰማ ነበር:: ጥቂት ቆየት ብሎም ሳያስበው ያንኑ በግንቦቱ ምርጫ ወቅት ያምታታበት የነበረውን ማምለጫ “ወያኔ መቼም እብድ ካልሆነ የታጋዮችን ቤተሰብ ይተናኮላል አልልም” ብሎት አረፈው:: ቀጥሎም በደመ ነፍስ የተናገረውን ከድንጋጤው ወጥቶ ሲያስበው ትዝብት ውስጥ እንደሚከተው እንደተጋለጠም ሲረዳው አድሚኗን አቋርጦ ተጨማሪ አለኝ በሚል አይነት “ታጋይ፥ ቤተሰቤን፤ ማቄን፤ ጨርቄን፤ አይልም” የሚል በጭራሽ የሱ ያልሆነ ቀረርቶ ቢጤ ውሸት ዋሽቶ ራሱን ሸውዶ አልፏል:: በተደጋጋሚም ስላለፈው ነገር አታንሱብኝ ሲል ወትውቷል:: የትላንቱ ከተረሳ ወደፊት መራመድ የማይሆን መሆኑን የተረዳው አድማጭ ግን ለዚህ ሳይበገር በጥያቄ አፋጦታል:: ብርሃኑ ላለፉት አስራ አምስት አመታት እሱና መሰሎቹ ወያኔን ዲሞክራሲያዊ ሽፋን እየሰጡ እዚህ ደረጃ በማድረሳቸው ይቅርታ ይጠይቅ እንደሆን ሲጠየቅ ለመሆኑ ይቅርታ የሚጠየቀው ማነው የሚል ትእቢት የተሞላው ምላሽ ሰጥቷል:: ለብርሃኑ ኢትዮጵያ ባለቤት የሌላት ሀገር ናት ወይም ባለቤቷ እሱ ነውና የፈለገውን ያደርጋታል::

አንዳርጋቸው ጽጌ ከረንት አፌይርስ በተባለው ሩም ስለወቅቱ ሁኔታና ስለቀጣዩ ጊዜ የሰጠውን ማብራሪያ ለሰማን ሁሉ ግለሰቡ አጅሬ አንዳርጋቸው ባይሆን ኖሮ የድል ድግስ መደገስ በጀመርን ነበር:: ወያኔያዊ ታሪኩን እንኳ ረስተንለት፥ ድህረ ምርጫ አፍራሽ ሚናውን ብናስታውስ ይህን ሁሉ የሚቀባጥረው፥ ፖለቲካውን ያመሰው፤ የውጭውን ቅንጅት ያደባየው፤ በኢትዮጵያውያን ድርጅቶች በተለይም ህብረትና ቅንጅት መሀል የህብረት ትግል እንዳይካሄድ፤ ይባስ ብሎም ኢትዮጵያዊ አይደለንም ኢትዮጵያዊነት ዳግም መ*ተርጎም አለበት ከሚሉ ፀረ ኢትዮጵያ ሀይሎች ጋር ግንባር የፈጠረው፤ ቅንጅት ተጠናክሮ ትግሉን በተገቢው ወቅታዊ መፈክር ስር እንዳይቀጥል ታሪክ ይቅር የማይለው ግፍ በሀገርና በህዝብ ላይ የፈፀመው አንዳርጋቸው መሆኑን ላፍታም ቢሆን ያስረሳል የፓልቶክ ቀረርቶው:: ዳሩ አንዳርጋቸው ነውና ሌላ ብላ ብለን አልፈነዋል::

ዶር ብርሃኑ ንግግሩ በተቃርኖ የተሞላ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ አረፍተ ነገር ሌላ ጥርጣሬና ጥያቄ ይፈጥራል:: ጥያቄ መፍጠር ሲባል ደግሞ ያምኑት ለነበሩትም አጠያያቂ መሆን ማለት ነው:: ብርሃኑ ለምን የሙት ከተማ አድማውን እንዳከሸፈው ሲጠየቅ ካድማው ቀጥሎ ስለሚሆነው ነገር ዝግጅት ስላልነበረን ነው ብሏል:: በማግሥቱ ግን ከረንት አፌይርስ በተባለው ፓልቶክ ሩም ደግሞ ለምን ከምርጫው በኋላ ሊፈጠር ይችል የነበረውን ሁኔታ አልገመትክም ሲባል ምርጫውን እንደምናሸንፍ እርግጠኞች ስለነበርን ነው ብሏል:: ይህ ግለሰብ ነው ዋሺንግተን ዲሲ ቁጭ ብሎ በትጥቅ አመፅ ነፃ የሚያወጣን::

ብርሃኑ ያሁኑንና የግንቦቱን ትግል ሲያነፃፅር የግንቦቱ ምርጫ የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥ ያሁኑ ግን ሰብአዊ ክብርን ለማስመለስ (ዲስ ኢንፈራንቻይዝ ተደርገናል ኢንፍራንቻይዝ ለመሆን ይለዋል እሱ) ነው ይላል:: ብርሃኑ አውቆ ካልተሸወደና ይህን ያህል ለፖለቲካውና ለተጨባጩ ሁኔታ ባእድ ከሆነ ውነትም እንድ ግለሰብ ከዚህ ቀደም እንዳሉት ዲሜንሺያ እየተጫወተበት እንደሆነ ያሳምናል:: ይታያችሁ ወያኔ የህዝባችንንና የሀገራችንን ሰብእና ማዋረድ የጀመረው እንደብርሃኑ ሃሳብ ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ መሆኑ ነው:: ለዚህም ነው አንድ የፓልቶኩ ተሳታፊ ወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ የነበረው ከሰላሳ አመታት በፊት ሲመሰረትና ኢህአፓን ከትግራይ መሬት ይውጣ ካለበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ገልፆ ያፋጠጠው::

ብርሃኑና አንዳርጋቸው የግንቦቱን ህዝባዊ አመፅ አኮላሽተው ህዝብ እጅ ውስጥ ሊገባ የተቃረበን ድል አስቀምተው ተንገዳግዶ ብርክ ይዞት የነበረውን የወያኔ ቡድን ኦክሲጅን አቀብለው ነፍስ እንዳልዘሩለት ሁሉ ዛሬ ደግሞ ደምስሰነው ልንገላግልህ ነው አባባላቸው ውሸትነቱን ላፍታ እንኳ ባንጠራጠርም እንቅስቃሴያቸው ግን የጀርባ ሴራ እንዳለው በርግጠኝነት መናገር ይቻላል::

የሁለቱንም ግለሰቦች ንግግር በጥሞና ላደመጠ አንድ እያሴሩ ያሉት አደገኛ ጉዳይ ቢኖር ድርጅት እኛ ብቻ ነን ሌሎች ድርጅቶች ፈርሰው በሥራችን ይጠቃለሉ የሚል ነው:: ይህንንም የሚገልፁት ባሁኑ ወቅት ፓርቲዛን ፖለቲካ አያስፈልግም በሚል ጤነኛ መሰል አባባል ነው:: ይህንኑ ጉዳይ ዶር ብርሃኑ 'ሁሉም ድርጅት ባንድ እዝ ሥር መጠቃለል አለበት' ሲል በትእዛዝ መልክ አረጋግጦታል:: ሃሳቡ በግልብ ሲታይ በጎ ይመስላል እንዲያውም የሚፈለገውና የታጣው ይህ ነበረ ያሰኛል:: ይሁን እንጂ በመጀመሪያ ማንኛውም ህብረት እኩልና ነፃ በሆነ ሁኔታ ሁሉም ወገን ተስማምቶ የሚመሰረቱት ተቋም እንጂ ማንም ከሆነ ጥግ ብቅ ብሎ ኑና በሥሬ ተሰባሰቡ በኔ እዝ ሥር ውደቁ ማለት ቢያንስ ፀረ ዲሞክራሲያዊ መሆን ነው:: ለዛውም መሪ ነን ባዮቹ ብርሀኑና አንዳርጋቸው መሆናቸው ሲሆን ትላንት የሰሩት በደል ከህዝብ አእምሮ ሳይጠፋ ዛሬም ይህን የፈረደበት ህዝብ ዳግም ሊሸጡት ዝግጅቱን ተያይዘውታል:: ይህ ማለቂያ የሌለው የሀገራችን ፖለቲካዊ ምፀት ነው:: በታኞች በምንም መልኩ አደራጅና መሪ የመሆን ሞራላዊ ብቃት የላቸውም:: ውሻን ለሥጋ ቤት ዘበኝነት ማመን ይቀላል:: የብርሃኑና አንዳርጋቸው የወቅቱ ዘመቻ መሰረታዊ አላማ ባንድም በሌላም በኩል ወያኔን ከተቻለ ባለበት ሁኔታ ካልተቻለና የህዝብ እምቢተኛነትና ትግል ካየለ ሥርአቱ በተለየ መልክ እንዲቀጥል (ሥርአቱን ለማዳን) ምናልባትም መለስ የሌለበት ሌላ ወያኔያዊ አምባገነን ሥርአት መፍጠር ሲሆን:: ይህንንም ለማከናወን ከሚጠቀሙበት ዘዴ ውስጥ:-

በውጭ ያለውን የተደራጀም ሆነ ያልተደራጀ የተቃዋሚ ሀይል 'ህብረት' በሚል ሽፋን በሥራቸው አሰባስበው እነሱ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ብቻ እንዲነጉድ ወይም ምንም አይነት ሀቀኛ የሆነ ፀረ ወያኔ የትግል መስመር እንዳይከተልና ሊካሄድ የሚገባውን እውነተኛ ትግል በውሸት ትግል በመተካት ህዝብን ውዥንብር ውስጥ ከቶ ትግሉን ማልከስከስ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ሌሎች ከነሱ ጋር የማይስማሙ ሀቀኛ ፀረ ወያኔ ሀይሎችን እንቅስቃሴ በማዳከም ብቸኛ ድርጅት ለመሆንና ትግሉን በሞኖፖል ይዞ አማራጭ ለማሳጣት ነው:: ይህ በመሰረቱ እነብርሃኑ ባለፉት በርካታ አመታት በተለያየ መልኩ ያራምዱት የነበረ የተካኑበት ጉዳይም ነው:: የብርሃኑና አንዳርጋቸው የቅርብ ጊዜ ታሪክም የሚነግረን ይህን ብቻ ነው::

እያንዳንዱ ህብረተሰብ ተገቢ መሪውን ያገኛል የሚል አባባል አለ:: እነብርሀኑም ሆኑ መሰሎቻቸው በህዝብና በሀገር ያሁንና የወደፊት ዕድል በተደጋጋሚ ሊነግዱ የሚችሉት ህዝብ እስካልታገላቸው ድረስ ብቻ ነው:: ስለዚህም ሁላችንም በያለንበት ልናጋልጣቸውና ልናስቆማቸው ይገባል:: ታሪኩን የረሳ፤ ከስህተቱም ያልተማረ ሊደግመው ይገደዳል እንዲሉ ትላንት እልፍ አእላፍ ወገኖች የተሰዉለትን ትግል ያኮላሹ ዛሬ መልካቸውን ቀይረው ዳግም ሊያደናቅፉን ሰዘጋጁ በቸልታ ማየት የህዝባችንን ስቃይ ማራዘም ለሚሹ ዕድል መስጠት መሆኑን ማወቅ አለብን::

የህዝብን መከራ የሚያራዝሙ የታሪክ ፍርድ ይጠብቃቸዋል
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

nathanbeniamin@yahoo.ca